# የወንጌል ምስክርነት አጀማመር

ወንጌልን ላልሰሙት ለመመስከር ከመውጣት በፊት ከመጸለይ ባሻገር፣ የተወሰነ ዝግጅት ማድረግ ጠቃሚ ነው።

ወንጌልን ለመመስከር የአጀማመር መንገዶች፡-

ልምዱ ከሌለ ወንጌል ለመመስከር ይፈለግና ሰው ጋር ሲገናኙ እንዴት መጀመር እንደሚገባ ግር የሚልበት ጊዜ አለ። ስለዚህ ላገኙት ሰው ምንም ሳይቸገሩ በቀላሉ ለመመስከር እንዲቻል እንደ ሚከተለው ራስን ማለማመድ ይጠቅማል። ከዚህ በታች ከሰፈሩት የምስክርነት አጀማመር መንገዶች ከመጠቀም በፊት ሁል ጊዜ በአክብሮት ሰላምታ ከማቅረብ መነሳት ያስፈልጋል።

1. አጠቃላይ ጭውውትን ወደ መንፈሳዊ ጭውውት መለወጥ።
   ዮሐ 4፡7፣ ጌታ ኢየሱስ ውሃ ልትቀዳ ወደ ውሃ ጉድጓድ የመጣችውን ሳምራዊት ሴት "እባክሽ የምጠጣው ስጪኝ" በማለት ጀምሮ ወደ ወንጌል መልዕክት መለወጡ። ዮሐ 4፡10፣"ውሃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑን ብትረጂ ኖሮ… እርሱም የሕይወትን ውሃ ይሰጥሽ ነበር፤" ከዚያም እስከ ቁ. 26 ድረስ ከእርሷ ጋር እየተነጋገሩ ቀጠሉ። ቆየት ብሎ ሌሎች የሰማርያ ሰዎች ተጨምረውበት ምስክርነቱ እየሰፋ ሄደ። ዮሐ 4፡28-29-30፣ 39-42፣
2. ያገኙት ሰው በጊዜው እያደረገው ካለ ነገር በመነሳት፡- ሐ/ሥ 8፡30፣ ፊሊጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ የኢሳያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰምቶ "የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" በማለት እንደ ጀመረ ያሳያል።
3. ሊመሰክሩለት የፈለጉት ሰው ጋር ተያያዥ የሆነ በአካባቢው በሚያዩት/ካዩት ነገር በመነሳት፡ ሐሥ 17፡16፣ 22-23። ሐዋሪያው ጳውሎስ በአቴና ከተማ ውስጥ ሲዘዋወር ከተማይቱ በጣዖታት የተሞላች መሆንዋን ስላየ ያንኑ ለወንጌል ምስክርነት ከእንደ መነሻ አድርጎ ተጠቀመበት።
4. ከእግዚአብሔር ቃል አንደ ተማሩት በመኖር/በአኗኗር/የሕይወት ምስክርነት፡ - ብዙ ፍሬ ብታፈሩ ሰዎች ደቀመዛሙርቴ መሆናችሁን ያውቃሉ።
   የተማሩትን የእግዚአብሔር ቃል በስራ ላይ በማዋል (እንደ ተማሩት ቃል በመኖር) በየጊዜው መልካም ፍሬ እያፈሩ የባሕርይ ለውጥ በማሳየት እያደጉ መሄድን የሚያዩ ሰዎች፣ በሚያዩት መልካም ስነ-ምግባር ደስ እየተሰኙ እነርሱም ወንጌልን ወደ መከተል እንዲሳቡ ያደርጋል። ማቴ 5፡16፣ ዮሐ 13፡34-35፣15፡8፣ 8፡31፣
   ይሄ ዋናው የምስክርነት ዓይነት ተደርጎ ሊወሰድ የተገባ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ቃል እንደ ተማረው ሲኖር/ሲተገብር በመንፈስ ቅዱስ ዘወትር እየተሞላ ስለሚሆን የምስከክርነቱ ቃል ኃይል ያለው ይሆንና የብዙዎችን ልብ ይማርካል።
5. መስካሪው ራሱ በወንጌል ካለማመን ወደ ማመን እንዴት እንደ መጣና ካመነ በኋላ በሕይወቱ ጌታ ካደረገለትን መልካም ነገሮች ዋና ዋናዎቹን በማንሳት ላልዳነው ሰው መመስከር። የራስ የዳኑበት ሁኔታ ከመዳን በፊትና በኋላ የሚታይ ለውጥ ዘርዘር አድርጎ የመናገር ምስክርነት፣ ሐሥ 22፡1-15፣ 26፡9-20፣ዮሐ 4፡28-29-30፣ 39-42፣

ይሄ ጉዳይ ከ10 ደቂቃ በላይ ሊወስድ ስለሚችል በቂ ጊዜ እንደ ሚያገኙ ሲያውቁ ብቻ መጀመር ያለበት ነው።

6. በተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮችና አነስተኛ ሆቴሎች የሚሰሩ ሰዎችን ወደ አንድ ዕቃ/ምግብ በማመልከት ይሄ በነጻ የሚሰጥ ነው አይደል? ወይም ከእነዚህ ዕቃዎች በነጻ የሚሰጠው የቱ ነው? ሲባሉ በመደነቅ እየተመለከቱ በነጻ የሚሰጥ አይደለም በማለት ሲመልሱ፤ ያኔ መስካሪው በነጻ እንደ ማይሰጥ አውቃለሁ፤ ነጋዴዎች በነጻ ለማደል ሱቆች አይከፍቱም። ነገር ግን እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ስጦታ የሆነውን የዘላለም ሕይወት በጌታ ኢየሱስ አማካይነት በነጻ እየሰጠ ነው እያሉ ወደ መመስከር ማዞር።
7. የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት/በመጠየቅ መጀመርና ወደ ምስክርነት መግባት፡ ምሳሌዎች፡ -

7.1. የጌታን ስሞች ለምስክርነት መጀመሪያነት መጠቀም። መዳኒት ጋር፣ ትንሳኤ ጋር፣ ሕይወት ጋር፣ ሰላም ጋር ...ወዘተ ትተዋወቃላችሁን? ማቴ 1፡21፣ ዮሐ 11፡25፣ ትንሳኤና ሕይወት፤ ኤፌ 2፡14፣ ሰላም፣...ወዘተ።
መድኃኒት ጋር ትተዋወቃላችሁን? ብለው ከጠየቁ በኋላ የቱ መድኃኒት? ብለው ሲመልሱ፣ ከስሙ ጋር የተያያዘውን ሙሉ ጥቅስ በመጥቀስ ስለ ጌታ ኢየሱስ አዳኝነት መመስከር።

7.2. የበጉ ሰርግ ለምስክርነት መጀመሪያነት መጠቀም። የሰርግ ጥሪ ደርሶት ይሁን አይሁን በመጠየቅ.. ራዕ 19፡7፣ የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ... የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ በጌታ ኢየሱስ ያመኑት አማኞች ስብስብ ከጌታ ጋር ለዘለዓለም በሕይወት እንደ ሚኖሩ መመስከር ይቻላል።

7.3. ከሰላምታ ቃል በኋላ ጥያቄ በማቅረብ፣ ሥራ እንዴት ነው፡- ለሚጠፋ እንጀራ አትስሩ፣ ነገር ግን የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር ምግብ ሥሩ፤ (ዮሐ 6፤27) በማለት ወደ ምስክርነት መግባት፤

7.4. ኑሮ እንዴት ነው ...... በዚህ ምድር ጥቂት ጊዜ ለምንኖረው ኑሮ በቀን ብዙ ሰዓታት (በሺፍት በሚሰራባቸው አገሮች 2 ሺፍት) ሳምንቱን በሙሉ በመስራት እንደክማለን ግን ለዘላለም ህይወትስ ምን እያደረግን ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ የአዳኛችን ጌታ ኢየሱስ ማንነት በሚገባ እናውቃለን ወይ? በማለት ወደ ምስክርነት መግባት፡፤

7.5. አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ካንተ/ቺ ጋር ለመነጋገር ቢፈልግ እንዴት እንዲቀርብህ/ሽ ትወዳለህ/ጃለሽ። እንዴት ቢቀርብህ ይሻላል/ሊቀርብህ ይገባዋል ትላለህ?

7.6. ከዚህ በፊት ማንኛውም ሰው ስለ እግዚአብሔር ለመነጋገር ቀርቦህና አነጋግሮህ ያውቃል ወይ?

7.7. ስለ ወንጌል ስትሰማ ወደ አእምሮህ የሚመጣው ምን ዓይነት አሳብ/ቃል ነው?

7.8. አንድ ሰው ክርስቲያን የሚሆነው እንዴት ነው ብለህ ታስባለህ?

7.9. ከእግዚአብሔር ጋር በግል መተዋወቅ የሚቻል ይመስልሃል?

7.10. ከእግዚአብሔር ጋር ቀረቤታ/ተዛምዶ ስለመፍጠር መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ያሳየህ/ያብራራልህ ሰው አለ ወይ?

7.11. በልጅነት እድገትህ ሂደት በምን ዓይነት ሃይማኖት ውስጥ አልፈሃል?

7.12. እንደዚህ ብዙ ሃይማኖት በምድራችን ያሉት ለምን ይመስልሃል፡፡ ሁሉም ትክክልና ሊያድኑ ይችላሉ ብለህ ታስባለህ ወይ?

7.13. ሰው የዚህ ዓለም ኑሮው ሲፈጸም/ሲያልቅበት ምን ይሆናል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰሃል?

7.14. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዘላለም ሕይወት ምን እንደሚል አስሰኸው ታውቃለህ ወይ?

7.15. እግዚአብሔርን አምኖና ለእርሱ ተገዝቶ ለመኖር በጣም ያስቸግራል የምትለው ምክንያት አለ ወይ?

7.16. የአንድ አገር/የዓለም ነዋሪ ሕዝብ እርስ በርሱ ተስማምቶና ተከባብሮ መኖሩ እንዲያድግ ያስችላል የምትለው አንድ ነገር ምንድነው? ፍቅር

ወንጌል ሊመሰክሩለት የፈለጉት ሰው ለመስማት ፈቃደኛ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ከፈለጉ፣ ወንድሜ/እህቴ፣ አንድ ጥያቄ ብጠይቅ ፈቃደኛ ኖት? አዎን ካለ፣ ጥያቄዬ መንፈሳዊ ነው ካሉ በኋላ ከተስማሙ ጥያቄውን መጀመር ይቻላል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ከተጀመረ ለምን መንፈሳዊ ጥያቄ አነሳህብኝ ብሎ ወደ መቆጣት እንዳይገባ ያግዛል፡፡

**ትራክት በመስጠት ወይም በቃል ምስክርነት የሚከናወን ከሆነ ማንኛውም ትክክለኛ የወንጌል ምስክርነት መልዕክት 4 አስፈላጊ ጉዳዮችን** አካቶ የያዘ ቢሆን መልካም ነው፤ እነዚህም፡ -

- ያልዳነ ሰው ሕይወት በኃጢአት የተበከለ ቢሆንም እግዚአብሔር አንተን/አንቺን ጨምሮ ሰውን ሁሉ የሚወድ መሆኑን መናገር፣ ዮሐ 3፡16፣ 10፡10፤
- የኃጢአት ዋጋ የዘላለም ሞት በመሆኑ፣ መዳን የሚያስፈልግ ስለ መሆኑ፣ ሮሜ 3:23, 6:23፤
- በነጻ የተሰጠ የመዳን መንገድ ኢየሱስ መሆኑንና ለምን ኢየሱስ ብቻ እንደሚያድን፣ ጌታ ኢየሱስ አምላክ ሆኖ ሳለ ስለ እኛ ሰው ሆኖ ስለ ኃጢአታችን ብዙ መከራ በመቀበል መሞቱና በ3ኛው ቀን መነሳቱ፣ 2 ቆሮ 5:15, ዮሐ 3:14-16፤
- ለመዳን የሰው ድርሻ ምን እንደ ሚጠበቅበት/ማድረግ እንዳለበት የሚያሳይ (ማሳየት የሚችል)፡- ንስሃ መግባትና በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፣ ሮሜ10:9-10፤